# ዕሳት ላይ ተቀምጦ

አንደኛ በግንቦት ወያኔ ሲገባ
በሰኔ ወር ደግሞ በጊወን ስብሰባ
በግሉ ወሳኔ ድንበራችን ቆርሶ
ኤርትራን ለሻቢያ በፊርማው አውርሶ
ካንዴም ሁለት ሶስቴ
እየተከተለ የወያኔን ኮቴ
በሰጠነው ስልጣን ሀላፊነት ሁሉ
ኢየሱስን ጴጥሮስ እንደ ከዳው ቃሉ
ብሄራዊ ክህደት
የሠራው ?ሀ? ብሎ
ጴጥሮስ በዚያች ዕለት
ስልጣን ተቀብሎ
ያማራጭ ሀይሎችን
ቀብሯል በቁም ገድሎ!!
ሁለተኛ ደግሞ
ገንጭና አረማሞ
ለመሪነት መርጠን
መሾሙ ሳያንሰን
ፓሪስም ጋብዘን
ለዕምነት_አልቦነቱ ለከሀዲ ቃሉ
በዘር ለወረሰው ወይም ከባህሉ
ለክህደት ወሮታ ሽልማት ይመስል
እንደገና ሹመን ትግሉን እንዲገድል
እኛም ፈፅመናል ስም የሌለው ወንጀል።
አሁንም ሳንማር ደግመን ለሶስተኛ
የወያኔን ሰላይ የፈረንጅ ቅጥረኛ
ለሆዱ አደር ባንዳ ሀሞተ_ቢስ ፈሪ
ሊቀመንበር አርገን የህብረቱ መሪ
ባመፅ ችንካር ካስማ
በሙት ከተማ አድማ
ትግል ያለ መሪ በጭራሮ መዝጊያ

ድል ለመቀዳጀት ያለምንም ውጊያ

ወላይታ? ጉርጂ?. ሶዶና ሀድያ

እበላ ባይ ቡከን ለመሪነት መርጠ

ሲቃጠል ያለቅሳል ዕሳት ላይ ተቀምጠ!!!

ሚያዚያ 1998

abraham beyenne